# ዓለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማህበር

## ህዝብ ለህዝብ አይፋጅም !

ዛሬ አገራችን ወስጥ የህዝብ ጠላቶች ህዝብ ለህዝብ በማፋጀት የሥልጣን እድሜያቸውን ለማራዘም ከፍተኛ ሴራ በመወጠን በተግባር ለመተርጐም እየተራወጡ ይገኛሉ ። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን እርኩስ ሴራቸውን ለማክሸፍና ኢትዮጵያን ለማዳን የጀመረው ትግል ድል እንደሚጎናጸፍ ፍጹም አንጠራጠርም ። ማህበራችንም ይህ አገርና ህዝብ አጥፊ ቡድን የለኰሰውን ህዝብ ለህዝብ የማፋጀት ውጥን ለመመከትና አገራችንን ለመታደግ ከወገኑ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን ተሰልፏል ። ህዝብን ከፋፍሎ የማፋጀት ሴራ ለማምከንም ከዴሞክራሲያዊያን ኃይሎች ጋር ትግላችንን ለማቀናጀትም ወስነናል ።

እኛ በኤውሮጳ ፣ በአሜሪካ ፣ በካናዳና አውስትራልያ የምንኖር "ዓለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማህበር" አባላት ፣ በአሁኑ ጊዜ የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ በህዝባችን ላይ ፣ በተለይም በአዲስ አበባ ህዝብ ላይ የሚያካሂደውን አረመኔያዊ ግድያ እጅግ አሳዝኖናል ፣ አስቆጥቶናልም ። ይህ የተፈጸመውና በመፈጸም ላይ ያለውን ወንጀል አጥብቀን እያወገዝን ፣ ለወንጀሉ ተጠያቂዎችም መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ መሆናቸውን በማያሻማ መንገድ ለመግለጽ እንወዳለን ።

ይህ ህወሓት/ኢህአዴግ በአሁኑ ጊዜ የሚያካሂደው ጭፍጨፋ ፣ ህዝባችን በግንቦት ወር ምርጫ ከሥልጣን ውረድ ብሎ የሰጠውን ዴሞክራሲያዊ ውሳኔና ፍርድ ለመቀልበስ መሆኑ ጥርጥር የለውም ። እንደሚታወቀው በግንቦት ወር በተካሄደው ምርጫ በህወሓት/ማሌሊት ግልገል ፋሽሽቶች አገዛዝ ሥር ሙሉ ለሙሉ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቱ ተረግጦ በባርነት ከሚኖረው የትግራይ ህዝብ በስተቀር በሌላው የአገራችን ግዛቶች ህወሓት/ኢህአዴግ አሳፋሪ ሽንፈት መከናነቡ ይታወቃል ። ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን ያሟላ ምርጫ ቢካሄድ ትግራይ ውስጥም አንድ ወንበር ማሸነፍ እንደማይችል የህወሓት/ማሌሊት አመራር በሚገባ ተገንዝቦታል ። የህዝብን መብት አፍኖ በብቸኝነት "ተወዳዳሪ" ሆኖ መቅረቡ የሚመሰክረውም ይህንን ነው ። ህወሓት/ኢህአዴግ በተለይ ብዙ ብሔሮችና ብሔረሰቦች በፍቅርና በአንድነት በሚኖሩባት ርእሰ ከተማችን አዲስ አበባ አንድ ወንበር እንኳ ሳያገኝ ተዘርሯል ። ህወሓት/ኢህአዴግ የአዲስ አበባ ሽንፈቱን ለጊዜው የተቀበለው ፣ የውጭ አሳዳሪዎቹን ወቀሳና የአዲስ አበባ ህዝብ ቁጣን በመፍራት ቢሆንም ፣ በአማራ ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎች ግን የተቃዋሚ ኃይሎች አባላትና ታዛቢዎችን በማሰር ፣ በመግደልና እንዲሁም የምርጫ ኮሮጆዎችን በመዝረፍ "አሸናፊ ነኝ" ፣ እያለ ነው ። የራሱ ቅጥረኞች የሆኑት የምርጫ ቦርድ ተብዬ አባላትም የዚህ ወንጀል ተባባሪ በመሆን "አሸናፊነቱን" ሊያፀድቁለት በመሯሯጥ ላይ ናቸው ።

የህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች ምርጫውን እንደሚያጭበረብሩ መጀመርያውኑም የሚያጠራጥር አልነበረም ። እነዚህ የስታሊንና የኤኒቨር ሆጃ ደቀመዛሙርት ምርጫ ውስጥ የገቡት ከላይ እስከታች ስታሊናዊ በሆነ መዋቅር ህዝቡን በተለይም የገጠሩን ህዝብ ስለሚቆጣጠሩት ፣ ገፋ ቢል ለተቃዋሚዎች ጥቂት የፓርላማ መቀመጫዎች (ወንበሮች) በመስጠት በዴሞክራሲያዊ መንገድ ተመረጥን ብለው "ህጋዊነት"(Legitimacy) ለማግኘት እንደነበረ ጥርጥር የለውም ። በተለይ ደግሞ

ከደደቢት ጀምሮ "ከኔ በላይ ላሳር" የሚባል መርዛም ሥነልቦናዊ በሽታ የተጠናወተው ግልገል ፋሽሽት መሪ መለስ ዜናዊ ፤ ለውጭ አሳዳሪዎቹ ዴሞክራት መስሎ ለመታየት ፤ እነሱ የሰጡትን የተወሰነ ዓለም አቀፋዊ ዝና (International reputation) ላለማበላሸትና እንደ ከዚህ በፊቱ አንድ የደቡብ ኮሪያ ዩኒቨርሲቲ የቸረው ዓይነት ተጨማሪ "የክብር ዶክትሬት" ማዕርግ የሚለግሱ ዩኒቨርሲትዎች ቢገኙ ለማጭበርበር ነው ።

ይህ የግልገል ፋሽሽቶች እቅድ ሳይሳካ ቀርቷል ። በአንፃሩ ሳያስቡት ድንገት ደራሽ ህዝባዊ ማዕበል (ጎርፍ) ደርሶባቸዋል ። ይህንን ህዝባዊ ጎርፍ ለመግታትም አስመሳይ የዴሞክራሲ ካባቸውን አውልቀው አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ጀምረዋል ። ከዚህ አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ጎን ለጎን ደግሞ ህዝብ ለህዝብ ለማፋጀት ዘረኛ ቅስቀሳ በማካሄድ ላይ ይገኛሉ ። ከምርጫው በፊት የሩዋንዳውን ፍጅት በማጣቀስ ሲያካሂዱት የነበረውን ዘረኛ ቅስቀሳ አሁንም በስፋት ቀጥለውበታል ። የትግራይ ህዝብ በነሱ እጅ እንዳልተጨፈጨፈ በማስመሰል "የትግራይ ህዝብ አማራ ሊጨፈጭፍህ ተነስቷል" እያሉ በካድሬዎቻቸው በራሪ ወረቀቶች አዲስ አበባ ውስጥ እያስበተኑ ይገኛሉ ። ከዚህም በተጨማሪ ሆን ብለው የትግራይን ህዝብ ከወገኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ለማናቆር በብዛት ትግርኛ ተናጋሪዎች ያሉበት "አግአዚ" በሚባል ክፍለ ጦር አዲስ አበባን አስወርረው ህዝባችንን በመፍጀት ላይ ይገኛሉ ።

እኛ በኤውሮጳ ፤ በአሜሪካ ፤ በካናዳና አውስትራልያ የምንኖር ዴሞክራሲያዊያን የትግራይ ተወላጆች ፤ የህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች የሚያራምዱት የዘር ጥላቻ ቅስቀሳ ቢያሳዝነንም ፤ አያስገርመንም ። ምክንያቱም የህወሓት/ማሌሊት መሪዎች የሚያራምዱት የዘር ጥላቻ ቅስቀሳ አዲስ ክስተት አይደለምና ነው ። ይህንን የምንለው የህወሓት/ማሌሊት መሪዎች ፤ በተለይም "የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት" ምስረታ ማኒፌስቶ ደራሲያን መለስ ዜናዊ ፤ ስብሓት ነጋ ፤ አባይ ፀሓዬና ሥዩም መስፍን ገና ከጥንቱ ከጥዋቱ ከደደቢት ጀምሮ ሲያራምዱት የነበረ ቀጣይነት ያለው ቅስቀሳ መሆኑን ጠንቅቀን ስለምናውቅ ነው ። ስለሆነም እነዚህ "ሰዎች" ህዝብ ለህዝብ አጋጭተው ሥልጣናቸውን ለማራዘም የማይፈነቅሉት ድንጋይ ፤ የማያጠምዱት ወጥመድ ፤ የማይሸርቡት ሴራና አረመኔያዊ ድርጊት አይኖርም ። የትግራይ ተወላጅ ኢትዮጵያዊያንን በጅምላ በመግደል ፤ ንብረታቸውን በመዝረፍ ፤ በማዘረፍና በማቃጠል ፤ ይህንን የፈፀሙት "ኢንተርሀዋሜ" የተቃዋሚ ኃይሎች ናቸው ብለው ፤ ህዝብ ለህዝብ እንዲጋጭ አድርገው ፤ የተቃዋሚ ኃይሎች አባላትን አስረውና ገድለው ሥልጣናቸውን ሊያስጠብቁና የሥልጣን እድሜአቸውን ሊያራዝሙ እንደሚጥሩ በበኩላችን አንጠራጠርም ። ስለሆነም እነዚህ ወጀለኞች ደም አቃብተውን ከመጥፋታቸው በፊት መጥፋት አለባቸው ብለን ስለምናምን የሚከተለውን መልእክት ለማስተላለፍ እንወዳለን ።

## <u>ለትግራይ ህዝብ</u>

የትግራይ ህዝብን ሥነ ልቦና ፤ ሥነ አእምሮ ፤ እምነት ፤ ኢትዮጵያዊ ስሜት ፤ ባህልና መንፈሳዊ ሕይወት ሳይላበሱ ትግራይ ላይ በቅለው በትግራይ ህዝብ ስም አስመስለው የሚምሉት መለስ ዜናዊና ተከታዮቹ ፤ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብትህን ገፈው በስምህ እየዘረፉና እየነገዱ ከወገንህ የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ሊያናቁሩህ በመሞከር ላይ ከርመዋል ። አሁን ደግሞ ዙፋናቸው በህዝብ ማዕበል ሲናወጥ አንተን በመሣርያነት ተጠቅመው ከወድምህ/እህትህ ኢትዮጵያዊ ወገንህ ጋር ሊያፋጁህ ከፍተኛ ሴራ በመፈጸም ላይ ናቸው ። ትላንት ሻዓቢያ ጥቃት ሰንዝሮብህ ፤ የጥቃቱ ሰለባ ሆነህ ልጆችህ በሻዓቢያ አይሮፕላኖች ናፓል ቦምብ ሲጨፈጨፉ ካንተ ጋር ሆኖ የተዋደቀውን

ወንድም/እህትህ ወገንህ የአማራ ፤ የኦሮሞ ፤ የጉራጌ ፤ የከምባታ ፤ የሀዲያ ፤ የሶማሊያ ወዘተ ህዝብ ጋር ደም ሊያቃቡህ ከፍተኛ ሴራ እየጠነሰሱ ነው ። ስለዚህ ይህንን ተንኮል በተባበረ ክንድህ ለመምታት ተነሳ ። እነዚህ ግልገል ፋሽሽቶች ነገም እንደትላንቱና ዛሬ መብትህን ገፈው በአስከፊው ሥርዓታቸው ሥር እያማቀቁ ሊገዙህ የተዘጋጁ ነብሰ በላዎች እንጂ ችግርህን ለመቅረፍና የጭቆና ቀንበራቸውን ካንተላይ ለማንሳት የተዘጋጁ የፖለቲካ ስብእና እንደሌላቸው ከሁሉም ይበልጥ ጠንቅቀህ አንተ ታውቃቸዋለህ ። እኛ በውጭ የምንኖር ልጆችህም ችግርህ ችግራችን በመሆኑ ምንጊዜም ቢሆን ከጎንህ ለመቆም መቁረጣችንን ቃል እንገባለን ።

## ከትግራይ ውጭ በተለይ አዲስ አበባ ለምትኖሩ የትግራይ ተወላጆች

መለስ ዜናዊና ተከታዮቹ ከትግራይ ውጭ በተለይም በአዲስ አበባና በባህር ማዶ የሚነዙት የጥላቻ ቅስቀሳ በሚገባ ትገነዘቡታላቹህ ብለን እናምናለን ። በተለይ በአሁኑ ሰዓት የአገዛዙ የጥቅም ተካፋዮች በህዝባችን ደም ጥቅማቸውን ለማስከበር የሚነዙት አስመሳይ የህዝብ ተቆርቋሪነት እጅግ መርዘኛና ዘላቂ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጥቅማችንን እጅጉን የሚጎዳ መሆኑ ሁሉም ይገነዘበዋል ብለን እናምናለን ።
ስለሆነም የህወሓት መሪዎችም ሆኑ የጥቅም ተካፋይ መልእክተኞቻቸው የሚነዙት የጥላቻ ቅስቀሳን በመመከት እነዚህ ለናንተም ለትግራይም ፤ ለኢትዮጵያም ያልሆኑ ከሀዲዎች ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጎን በመሰለፍ ታግላቹህ እንድታስወግዷቸው እናሳስባለን ።

## ለአግአዚ ክፍለጦር አባላት

አብዛኞቻቹህ የዚህ ነፍሰ ገዳይ የጦር አባላት የትግራይ ተወላጆች የመለስ ዜናዊ ቅልብ ልዩ የጥበቃ ኃይል መሆናቹህን ለመገንዘብ ችለናል ። በዚህ ክፍለጦር ውስጥ ኤርትራዊያን ቅጥረኞችም እንዳሉበት መረጃዎች ደርሰውናል ። የመለስ ዜናዊን የሥልጣን እድሜ ለማራዘም በህዝባችን ላይ የምታካሂዱት ጭፍጨፋ እጅግ አሳዝኖናል ፤ አስቆጥቶናልም ። ለኛ ከመለስ ዜናዊ ጋር ሆኖ ህዝባችንን የሚጨፈጭፍ ከትግራይ ይምጣ ከሌላ ነፍሰ ገዳይ ነፍሰ ገዳይ ነው ። በመሆኑም እስካሁን የፈፀማችሁትን ወንጀል ተገንዝባቹህ ይቅርታ በመጠየቅ ከህዝባችን ጎን አብራቹህ በመሰለፍ ግልገል ፋሽሽቶችን እንድትፋለሙ እንመክራለን ። አለበለዚያ ነገ የመለስ ዜናዊ ሥርዓት ሲፈርስ እናንተም እንደምትፈርሱና በወንጀል እንደምትጠየቁ ማወቅ ይኖርባቹሀል ።

## ለተቃዋሚ ኃይሎች

የተቃዋሚ ኃይሎች የአመራር አባላትና ደጋፊዎች በአረመኔው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በሚደርስባቹህ እንግልት ፤ እስራት ፤ ድብደባና ግድያ ሳትበገሩ ለአገራችን አንድነትና ለዴሞክራሲ ግንባታ እየከፈላችሁት ያለው መስዋእትነትና የምታካሂዱት ትግል በታሪካችን አኩሪ ምዕራፍ ይይዛል ። ለመስዋእትነታቹህ ያለን ክብርና አድናቆትም ወሰን የለውም ። በመሆኑም መስዋእትነት በመክፈል ላይ ያላቹህ ዴሞክራሲያዊያን ወገኖቻችን ትግላቹህ ትግላችን ፤ ዓላማቹህም ዓላማችን ነውና ከጎናቹ እንሰለፋለን ።

የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ አሉላን የወለደ ህዝብ መለስ ቢበቅልበትም ፤ የትግራይ ህዝብ ወንድሙ/እህቱ (ወገኑ) መሆኑ የተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሚያውቅ አሳምረን እንረዳለን ። የመለስ ዜናዊ ህዝብን ከህዝብ የማፋጀት ሴራንም ከወገኑ የትግራይ ህዝብ ጋር ሆኖ እንደሚያከሽፍ ጽኑ እምነት አለን ። የመለስ ካድሬዎች እንደሚያደርጉት ፤

አናሳ ጽንፈኞችና ካፍንጫቸው ባሻገር ለመመልከት የማይችሉ የአእምሮ ጨቅላዎች ህዝባዊ ትግሉን አቅጣጫ እንዳያስቱ ሁሉም ነቅቶ እንዲጠብቅ ለማሳሳብ እንወዳለን ።

በመጨረሻም ለዴሞክራሲ ፣ ለሰብአዊ መብትና ለአገር አንድነት ቆመው ከአምባገነኑ የግልገል ፋሽሽቶች አገዛዝ ጋር ሲታገሉ ሰሞኑን በአዲስ አበባ ክቡር የሆነውን የህይወት መስዋእትነት ለከፈሉት ጀግኖቻችን ያለንን ክብርና አድናቆትን እየገለጽን ፣ የኢህአዴግ መሪዎች በፖለቲካ አመለካከታቸው በእስር ቤትና በቁም እስር የሚያሰቃዩዋቸውን ወገኖቻችንን ባስቸኳይ በነፃ እንዲለቁዋቸው አጥብቀን እንጠይቃለን ። በተረፈ በሰሞኑ ህዝባዊ ትግል በግፍ ተጨፍጭፈው መስዋእትነት የከፈሉ ወገኖቻችን ባገራችን ታሪክ ዘላለማዊ የክብር ስፍራ ይኖራቸዋል እያልን ለቤተሰቦቻቸውና ዘመድ አዝማዶቻቸው ፅናቱን ይስጣቹህ እንላለን ።

ውድቀት ለግልገል ፋሽሽቶች ሥርዓት ! ! !
ዴሞክራሲ ለኢትዮጵያ ህዝብ ! ! !
ታጋይ እንጂ ትግል አይሞትም ! ! !

ዓለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማህበር

ሰኔ 1997 ዓ.ም

Contact us on: itda2005@yahoo.com